## "ኢትዮጵያ ውስጥ ድርቅ እንጂ ረሃብ የለም" ማለት በህዝብ ህይወት ላይ ማፌዝ ነው

**(ከኦነግ ኢንፎ ዴስክ)**

የወያኔ ስርኣት የሚሊዮኖችን ህይወት ለሰቆቃ የዳረገውን የረሃብ ኣደጋ በማስተባበል "ኢትዮጵያ ውስጥ ድርቅ እንጂ ረሃብ የለም" በማለት ይቀጥፋል። በድርቁ ሳቢያ ሊከሰት የነበረውን የረሃብ ኣደጋ ለማስቀረት በቂ ቅድመ ዝግጅት በማድረጋችን ኣንድም ዜጋ ለረሃብ ሳይጋለጥ ልንቀለብሰው ችለናል በማለት በህዝብ ህይወት ላይ ይቀልዳል። ከእውነት የራቀ ዶኪመንታሪ ፊልም ኣቀነባብሮ በሚዲያዎቹ በማሰራጨት ጨርሶ ህላፊነት የማይሰማው ስርኣት መሆኑን ዳግም መስክሩዋል። በተከሰተው የድርቅና የረሃብ ኣደጋ ክፉኛ የተጎዱት የደቡብ ኦሮሚያ ነዋሪዎች መሆናቸው ግልፅ ነው። ወያኔ ከመሸበት በሁዋላ ኣቀነባብሮ በሚዲያዎቹ የለቀቀው የፕሮፓጋንዳ ፊልም የኣካባቢውን ነዋሪዎች የጎዳውን ሰውሰራሽ ኣደጋ ለመሸፋፈን እንጂ የኣደጋውን ክብደት ኣምኖ በመቀበል ኣግባብ ያለው መንግስታዊ እርምጃ ለመውሰድም ኣይደለም።

ለመሆኑ "ኢትዮጵያ ውስጥ ድርቅ እንጂ ረሃብ የለም" የሚለውን ፕሮፓጋንዳ ማራገብ በዚህ ወቅት ለምን ኣስፈለገ? መልሱ ግልፅ ነው። ከድርቁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ኦሮሚያ፣ ደቡብ ምስርቅ ኦሮሚያ፣ ምስራቅ ኦሮሚያ፣ በደቡብ ህዝቦችና በኦጋዴን ክልል ተንሰራፍቶ የሚሊዮኖችን ህይወት ስጋት ላይ ስለጣለው የረሃብ ኣደጋ ካሁን ቀደም ብዙ ተብሎኣል። ይህንን እውነታ የሚመሰክሩ ሪፖርቶች በኣንዳንድ ኣለም ኣቀፍ ሚዲያዎችና በእንደ ኦሮሞ ነፃነት ድምፅ ባሉ የታጋይ ድርጅቶች ልሳኖች በተከታታይ ቀርበዋል። እነዚህ ሚድያዎች የወያኔውን ስርኣት በሚያስበረግግ መልኩ ያለውን እውነታ ለኣለም ህዝብ ጆሮ ኣድርሰዋል። ከኣለም ኣቀፍ እውቅ የዜና ኣውታሮች ኣንዱ የሆነው ቢቢሲ "ኒውስናይት" በተባለው ልዩ ፕሮግራሙ በመረጃ ላይ ተደግፎ ባቀረበው ዶኪመንታሪ ፊልም የወያኔን መንግስት ማስከፋቱ ይታወቃል። በዚህ የቢቢሲ ሪፖርት መሰረት በኢትዮጵያ የተከሰተው ረሃብ በይበልጥ ሰውሰራሽ እንጂ ተፈጥሮኣዊ ኣይደለም። ለረሃብ ሰለባዎቹ ተብሎ ከውጭ ለጋሽ መንግስታትና ድርጅቶች የሚላከው እርዳታ ኣላማውን ስቶ ለመንግስት ፖለቲካዊ ፋይዳዎች እንደሚውል ተደርሶበታል። ከተራበው ህዝብ መሃል በስልጣን ላይ ያለውን ፓርቲ የማይደግፉ በቁጥር ብዙሃን የሆኑ ወገኖች እርዳታውን መነፈጋቸው ነው የተጋለጠው። ኣለም ኣቀፍ ለጋሾች በያመቱ ከ3 ቢሊዮን ዶላር በላይ ለኢትዮጵያ የሚያበረክቱ ቢሆንም ይህን ያህል ግዙፍ ገንዘብ ለተለገሰለት የልማት ኣላማ ሳይሆን ለስርኣቱ ድጋፍ መግዣና ስልጣን ላይ መሰንበቻ መዋሉ በዚሁ የቢቢሲ ሪፖርት ተመስክሮኣል።

ቢቢሲ ብቻም ሳይሆን እንደ ቪኦኤ ያሉ ሌሎች ኣለም ኣቀፍ ሚዲያዎችም በተለይም በደቡብ ኦሮሚያ የተከሰተው የድርቅና የረሃብ ኣደጋ ምን ያህል ኣስከፊ እንደነበር፣ በዚህ ሳቢያም የሰዎችና የቤት እንስሳት ህይወት መጥፋቱን ኣጋልጠዋል። የቪኦኤው ፕሮግራም ባልደረባ ሄኖክ ሰማግዚሄር ከሁለት ሳምንታት በላይ በደቡብ ኦሮሚያ የተለያዩ ስፍራዎች በመዘዋወር ያዘጋጀው ተከታታይ ዘገባ

ስርኣቱ ሊደብቃቸው የፈለገውን የሚዘገንን ኣደጋ በማጋለጥ ቀደም ሲል ቀርቦ የነበረውን የቢቢሲ ሪፖርት ኣጠናክሮኣል። በዚህ የቪኦኤ ሪፖርት መሰረት ከቦረና ከብቶች መካከል ከ70 ከመቶ በላይ የሚሆኑት በድርቁ ኣደጋ ሞተዋል። በደቡብ ኦሮሚያ ቦረና ዞን የሰው ልጅ የሚላስ የሚቀመስ በማጣት በድርቁ የጠወለጉትን የሰብል ቅጠሎች ከእንስሳት ጋር እየተሻማ ሲበላ ቪኦኤ በቪዲዮ የተደገፈ ሪፖርት በድረገፁ በማቅረብ የኣደጋውን ክብደት ኣጋልጦኣል። ሃገር ኣስተዳድራለሁ የሚለው የወያኔ መንግስት ግን ይህን ያህል የሚዘገንነውን ኣደጋ መሸፋፈን ይፈልጋል።

ኢትዮጵያ ባሏት የከብቶች ብዛት በኣላም ላይ 10ኛ በኣፍሪቃ ደግሞ የመጀመሪያውን ደረጃ እንደምትይዝ ይታወቅ ነበር። ኢትዮጵያ በከብቶች እርባታ በዚህ ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንድትታወቅ በማስቻሉ ረገድ ደግሞ በምርታማነታቸው የሚታወቁት የቦረና ከብቶች ቁጥር የጎላ ድርሻ እንዳለው ኣይካድም። ዛሬ ከነዚህ የቦረና ከብቶች መካከል ከ70 ከመቶ በላይ የሚሆኑት በድርቁ ኣደጋ መሞታቸው ነው እየተነገረ ያለው። ይህ ዜና በኢትዮጵያ ውስጥ በሃዘን እየተነገረ የሃገሪቷን ሚዲያዎች ትኩረት መሳብ ነበረበት። ይሁንና የቪኦኤው ኣማርኛ ፕሮግራም ባልደረባ በሃገሪቷ ተዘዋውሮ እንደታዘበው “*ደቡቡ የሃገሪቷ ክፍል በዚህ መሰሉ መጠነ ሰፊ ኣስከፊ ኣደጋ በሚመታበት ወቅት የመንግስት ሚዲያዎች በጉዳዩ ላይ ትንፍሽ ሲሉ ኣልተደመጡም። ለዚህ መጠነ ሰፊ ኣደጋ ሽፋን በመስጠት ፋንታ በኣባይ ግድብ ግንባታ ጉዳይ ላይ ትኩረታቸውን መጣል የመረጡ ይመስላሉ። ደቡብ ኦሮሚያ ውስጥ ዜጎች በከፋ ረሃብ ተጎድተው ሲያጣጥሩ ሸገር ላይ በኣዲስ ኣመት መግቢያ በኣል ጭፈራው ደርቷል።*”

እርግጥ ነው፣ በኣስር ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በከፋ ረሃብ ተጎድተው የወገን ያለህ እያሉ በሚያጣጥሩበት፣ የሃገር ኢኮኖሚ የጀርባ ኣጥንት የሆኑት በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ከብቶች ሞተው ለኣይን በሚሰቀጥጥ መልኩ ኣፅማቸው ሜዳውን ሞልቶ በሚታይበት ወቅት ሃገር እናስተዳድራለን የሚሉት የወያኔ ሹማምንት ፊንፊኔ ላይ በኣመት በኣል ፈንጠዚያ ተጠምደው ጮማ ሲቆርጡ ዊስኪ ሲራጩ ኣሳለፉ። የሃገራችን ኣካል ነው የሚሉት የቦረናው የከፋ ድርቅና ረሃብ ኣደጋ ኣላሳሰባቸውም። ኣደጋውን በተሳካ መልኩ ከኣለም ህብረተሰብ ጆሮ የሸሸጉት ይመስላቸዋልና በወቅቱ ኣልተረበሹበትም።

ስርኣቱ በብርቱ ሊሸሽግ የሚፈልገው እውነታ ስለተጋለጠበት ኣሁን በዝምታው መግፋት ኣልሆነለትም። በድንገት ከእንቅልፉ የባነነ ይመስል በደቡቡ የድርቅ ኣደጋ ላይ ጊዜ ካለፈበት በሁዋላ ሲያላዝን ተሰማ። “*ኢትዮጵያ ውስጥ ድርቅ እንጂ ረሃብ የለም*” በማለት ከላይ የተጠቀሱትን በማስረጃ የተደገፉ ሪፖርቶችን ለመቀልበስ ሲሞክር ሃፍረት ኣልተሰማውም።

ወያኔ በዚህ ጉዳይ ላይ በለብለብ ኣቀነባብሮ በሚድያዎቹ የለቀቀውን የሃሰት ዶኪመንታሪ ፊልም ተቀባይነት የሚያሳጡ በርካታ ነጥቦችን መዘርዘር ይቻላል። በዚህ የፕሮፖጋንዳ ፊልም ውስጥ በረሃብ ኣደጋው ምክንያት በከፋ መልኩ የተጎሳቆሉት ዜጎች ሆን ተብሎ ካሜራ ፊት እንዳይቀርቡ ተደርጓኣል። በመሰረቱ በከፋ ድርቅ ስለተመታ ኣንድ ኣካባቢ ሲዘገብ በዘገባው ኣካልነት የሚታቀፉት ምስሎች ጉዳትን እንጂ ድሎትን የሚተርኩ ሊሆኑ ኣይችሉም። በወያኔው

***የፕሮፓጋንዳ ፊልም ውስጥ ግን የሚታየው የዚህ ተቃራኒ ነበር። የአደጋውን ክብደት የሚያንፀባርቁ ጎስቁዋላ ሰዎች በሞሉበት ሃገር በጣት የሚቆጠሩ ሰውነታቸው ያልተጎሳቆለ ሰዎች ተፈልገው ካሜራው ፊት እንዲቀርቡ ነው የተደረገው። እነርሱም ቢሆኑ በኣፋን ኦሮሞ የተናገሯቸው ብሶትን የሚገልፁ ኣረፍተ ነገሮች በተሳሳተ መልኩ ተተርጉሞ መንግስትን በሚደግፍና በሚያመሰግን ሃሳብ ተመስሎ በኣማርኛ ተተረከ። የፊልሙ ምስላዊ ትኩረቶች በኣብዛኛው በከፋ ድርቅና ረሃብ የተጎዳውን ህብረተሰብና ኣካባቢው ሳይሆን የገበያ ውስጥ የእህል መሸመቻ ስፍራዎችና ሰፋ ሰፋ ያሉ የእርዳታ እህል መጋዘኖች ነበር። በፊልሙ የሚታዩት ከብቶች በኣብዛኛው በኣካባቢው የተከሰተውን ኣደጋ የሚገልፁ ኣይነት ሳይሆን በጣት የሚቆጠሩ ጥቂት በቂ መኖ የነበራቸውና ኣካላቸው ያልተጎሳቆሉት ናቸው። በመቶ ሺዎች ሞተው ኣፅማቸው በየሜዳው የሞላው ከብቶች ጉዳይ በፊልሙ እንዲታይ ኣልተፈለገም። የፊልሙ ኣላማ በእርግጥ የኣደጋውን ክብደት ለማውሳትና መንግስታዊ ሃላፊነትን ለመጠቆም ያለመ ቢሆን ኖሮ በስፋት የሚታየውን ኣስከፊ እውነታ ወደጎን ብሎ ያልተጎሳቆሉ ጥቂት ሰዎችና ከብቶችን ፈልጎ ባላተኮረባቸው ነበር። ነገር ግን ፊልሙ የወያኔ ፕሮፓጋንዳ ነውና ኣይፈረድም። ፊልሙ እውነታን ለመቀልበስ ያለመ ነውና ኣያስገርምም። ሃላፊነት የማይሰማውና የህዝቦቹ ቁስል እሱን የማይጠዘጥዘው መንግስት የሚነዛው ፕሮፓጋንዳ ነውና የተለየ ነገር የለውም። በጥቅሉ ከወያኔ የፕሮፓጋንዳ ፊልም እውነታን ፈልጎ ማግኘት ኣለመቻል የሚያስገርም ኣይሆንም።***

***መዘንጋት የሌለበት ሃቅ ግን የወያኔዋ ኢትዮጵያ በኣለም ኣቀፍ ነፃ ሚዲያዎች የሚተረትባት ጎስቁዋላዋ ሃገር እንጂ በስርኣቱ የፕሮፓጋንዳ ማሽኖች በድርብ ዲጂት እያደገች ነው ተብሎ በሃሰት የሚለፈፍላት ኢትዮጵያ ኣይደለችም። ብዙሃኑ የሃገሪቷ ድሃና ረሃብተኛ ህዝቦች የስርኣቱ ሚድያዎች ከስንት ሺህ ኣንድ ሁለቱን እየመረጡ ካሜራና ማይክራፎኖቻቸውን የሚደቅኑላቸው እጅግ ጥቂት በሆኑ ወገኖች የሚወከሉ ኣይደሉም። የህዝቦቹ የኑሮ ሁኔታም በነዚህ በጣት በሚቆጠሩ ምናልባትም በተራ ዜጋ በተመሰሉ የስርኣቱ ጥቅመኛ ካድሬዎች ቅጥፈት የሚገለፅ ኣይደለም።***

***ዛሬ ዛሬ እጅግ ብዙሃኑንና በስርኣቱ ኢ-ሰብኣዊ ፖሊሲዎች ሳቢያ ከሰውነት ተራ የወጡትን ዜጎች ለመገናኛ ብዙሃን በማቅረብ ብሶታቸውን በትክክል እንዲናገሩ ማስቻል ኣደገኛ ሆኖአል። የውጭ ሃገራት ነፃ ሚዲያዎች ሃገር ውስጥ እየተዘዋወሩ በመረጃ የተደገፉ ሪፖርቶችን እንዲያቀርቡ ስርኣቱ ኣይፈቅድም። እንዲያውም በመሰል ጥረቶች ላይ ተሳትፈው የተገኙት "ሽብርተኛ" የሚል ታፔላ ወዲያው ይለጠፍላቸዋል። በዚህ የይስሙላ ህግ ተወንጅለው ከተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር ሲያብሩ ተገኙ እየተባለ ይታሰራሉ። ሁለት የስዊድን ዜግነት ያላቸው ጋዜጠኞች በቅርቡ በኦጋዴን ክልል በሞያዊ ስራቸው ላይ ተሰማርተው ሳሉ ተይዘው መታሰራቸው ለዚህ ሃቅ በኣብነት ሊጠቀስ የሚችል ነው። ከዚህም በተጨማሪ በሃገር ቤት የሚንቀሳቀሱ የኦሮሞ ፓርቲዎች ኣመራር ኣባላት ለቢቢሲ ሪፖርተርና ለኣምኔስቲ ኢንተርናሺናል ወኪሎች መረጃ ኣቀበላችሁ ተብለው መታሰራቸው ሃቁን ይበልጥ ያጠናክረዋል።***

***በኢትዮጵያ የተከሰተውና የኣለም ህዝብ መነጋገሪያ ርእስ የሆነው የድርቁም ሆነ የረሃቡ ነገር ተፈጥሮኣዊ ሳይሆን በኣመዛኙ ሰው ሰራሽ ስለመሆኑ በሚገባ***

*አስምሮበት ማለፍ ያስፈልጋል። አደጋው ሰው ሰራሽ ስለመሆኑ አንድ ቀላል አብነት ማስቀመጥ ይቻላል። በቀደሙት ሁለቱ ስርኣቶች በኢትዮጵያ ተመላልሶ ይታይ የነበረው የረሃብ አደጋ ዛሬ በድርቅና በረሃብ ስማቸው ጎልቶ እየተጠቀሰ ካሉት ኣካባቢዎች የተለየ ነበር። ለምሳሌ ባለፉት ዘመናት በድርቅና በረሃብ አደጋ ከባድ ሰብኣዊ ጉዳት ከደረሰባቸው የሃገሪትዋ ኣካባቢዎች መካከል ትግራይ በቀዳሚነት ትጠቀስ ነበር። ዛሬ ግን ያ ታሪክ ሆኖ አልፎኣል። ምክንያቱም ትግራይ ዛሬ ለልማትዋና ለብልፅግናዋ በቁርጠኛነት የቆመላት መንግስት ኣላት። እንዲህ ማለት የትግራይ ህዝብ ለምን ከረሃቡና ከድርቁ አደጋ ተላቀቀ ብሎ ለመቆጨት እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል። በቀደሙት ስርኣቶች በድርቁና በረሃብ አደጋው ሲቀጣ የኖረው የትግራይ ህዝብ ዛሬ ከዚህ አደጋ መገላገሉ ኣስደሳች ዜና ነው። በምድራችን ላይ የሚኖር ማንኛውም ሰብኣዊ ፍጡር ከዚህ ኣይነቱ ኣስከፊ አደጋ ጋር ለዘላለም እንዲኖር የሚፈልግ ለህሊናው የሚገዛ ሰው ያለ ኣይመስለኝም።*

*ይሁን እንጂ ነፍስ ከማዳን ርብርብ ኣልፎ ይህን ኣስደናቂ ልማት ለኣንድ ክልል ብቻ ተግባራዊ አድርጎ የተቀሩትን መንፈጉና ብሎም ረሃብን እንደመቀጣጫና የዘር ማጥፋት መሳሪያ የመጠቀሙ ነገር ግን ከተጠያቂነት የሚያድን ኣይሆንም። ዛሬ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ስልጣን ጨምድዶ የያዘው ስርኣት የትውልድ ሃገሩ ለሆነችዋ ትግራይ በተለየ መልኩ መቆርቆሩ ላያስገርም ይችላል። የሚያስገርመውና የሚያሳዝነው ነገር ቢኖር ይህ ስርኣት ቀደም ሲል በልምላሜኣቸውና በለምነታቸው ይታወቁ የነበሩትን ኣካባቢዎች ዛሬ ወደ ከፋ ድርቅና ረሃብ ቀጣናነት መቀየሩ ነው። ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል፣ ኣርሲ በቀደሙት ስርኣቶች ሁሉ በዳቦ ቅርጫትነት የሚጠቀስ የኦሮሚያ ኣካባቢ ነበር። በተፈጥሮ ከለማውና ከለመለመው የኣርሲ ኣካባቢ ብቻ የሚመረት እህል የመላውን የኢትዮጵያ ህዝብ ኣመታዊ የቀለብ ፍጆታ ሸፍኖ እንደሚተርፍ በተደጋጋሚ ሲነገር ኖሩዋል። ዛሬ ግን ይህን መሰሉ የጥጋብ ተስፋ የሆነ ኣካባቢ ነው የተራበው።*

*በወያኔ ዘመን በድርቅና በረሃብ አደጋ መመታታቸው በጥናት የተረጋገጡ ኣካባቢዎች ኣርሲ ብቻም ኣይደሉም። በርካታ የምእራብ ሓረርጌና ምስራቅ ሓረርጌ ወረዳዎችም የአደጋው ሰለባ ሆነዋል። በምስራቅ ኦሮሚያ ድሮ ስለ ጥጋብና ብልጽግና ሲተርት ‘Rabbi duubaan Fadiis’ ይባል ነበር። ትርጉሙም “ከፈጣሪ ወዲያ ፈዲስ ኣለልን” እንደ ማለት ነው። ዛሬ በወያኔው ዘመን ግን እንዲህ ያሉ በምርታማነታቸው በምሳሌነት የሚጠቀሱ ኣካባቢዎች ተርበው ነዋሪዎቻቸው የእርዳታ እጅ ጠባቂዎች ሆነዋል። ምክንያቱ ደግሞ ግልፅ ነው። ኦሮሚያ እንደ ትግራይ የሚቆረቆርላት የራስዋ መንግስት የላትም። እንዲያውም በተቃራኒው፣ የለመለሙ ደኖችዋን ኣራቅቶ ምድረበዳ ያደረጋት፣ በተፈጥሮ የለማውን ኣፈሩዋን በመርዛማ ኬሚካሎች በክሎ ስነህይወታዊ እልቂት ያስከተለባት ጠላታዊ መንግስት ነው በሃይል የተጫነባት። በኦሮሚያ ዛሬ ሚሊዮኖችን ሰለባ ያደረገው የረሃብና የድርቅ አደጋ ሰው ሰራሽ እንጂ ተፈጥሮኣዊ ኣይደለም የምንለው ኣንድም ለዚህ ነው። ድሮ በድርቅ ቀጣናነታቸው የሚታወቁ ኣካባቢዎች ዛሬ ለምልመው፣ ለምለም የነበሩቱ ደግሞ መድረቃቸውና መራባቸው የተፈጥሮ ህግ ሳይሆን የሰው ልጅ የኣድሎኣዊነት ፖሊሲ ውጤት ነው። ዛሬ ኢትዮጵያን እያስተዳደርኩ ነው የሚለው ስርኣት*

ሁሉንም የሃገሪትዋ ክልሎችን በኣንድ ኣይን የሚመለከት መንግስት ስላለመሆኑ ሰሜኑንና ደቡቡን እያገናዘበ የቀረበው ኣጭርና ግልፅ መረጃ በቂ ኣብነት ነው።

የወያኔ መንግስት ፖሊሲ በንቀት የተሞላ እኩይ ፖሊሲ ስለመሆኑ ማስረጃ ዘርዝሮ መጨረስ ኣስቸጋሪ ነው። *"በኢትዮጵያ ድርቅ እንጂ ረሃብ የለም"* ከሚል መንግስት የበለጠ ኣስተዳድራቸዋለሁ ለሚላቸው ህዝቦች የከፋ ንቀት ያለው ስርኣት በኣለም ላይ ያለ ኣይመስልም። ይህ ንቀት ደግሞ ከከፋ ጥላቻ የሚመነጭ ነው። ጥላቻውም የስርኣቱን ጠላትነት እርቃኑን ኣውጥቶ ያሳያል። ጠላት ታዲያ ጠላት መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ዛሬ ባነገበው መሳሪያ በመመካት በህዝቦች ትከሻ ላይ ተጣብቆ ደማቸውን እየቦጠቦጠ ማበጡ ኣሌ የማይባል ነው። ኣንድ ቀን ግን እንደመዥገር ከተጣበቀበት የህዝቦች ትከሻ ተነቅሎ መወርወሩ ኣይቀሬ ነው።

ይህ ደግሞ የሚረጋገጠው የኦሮሞ ህዝብና የተመሳሳይ ጭቆና ሰለባ የሆኑ መላው የሃገሪትዋ ህዝቦች ህብረት ፈጥረው በቆራጥነት በመነሳት ፀረ ወያኔ ኣብዮት ሲያቀጣጥሉ ነው።

**ፍትህ ያሸንፋል!**

**የኦነግ ኢንፎ ዴስክ**